የCOLUMBIA (ኮሎምቢያ) ግዛት መንግስት
የከንቲባ Muriel Bowser (ሙሪየል ቦውዘር) የአፈጻጸም ቢሮ

Office of the Deputy Mayor for Health and Human Services (የምክትል ከንቲባ ቢሮ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች)

# ስለ ሕዝብ ሸክም መመሪያ አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቂዎች ለ DC ነዋሪዎች **

****አዲሱ የመጨረሻው የሕዝብ ሸክም መምሪያ በ NEW YORK (ኒው ዮርክ) እና የ WASHINGTON (ዋሺንግተን) ምስራቃዊ ግዛት የፌደራል ፍርድ ቤት በተሰጡ ሁለት ብሄራዊ ጊዜያዊ እግዶች ተለዋጭ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ታግዷል። ሕጉ በታቀደው መሰረት ኦክቶበር 15፣ 2019 ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።[1]**

*Washington (ዋሺንግተን)፣ DC ልዩነታችንን ያከብራል የስደተኝነት ሁኔታቸው ምንም ቢሆን ሁሉንም የ DC ኗሪዎችን ያከብራል። እኛ የመጠለያ ከተማ ነን ምክናያቱም እኛ ማንም ሰው ለእርዳታ የኛን መንግስት ጋር ለመደወል የማይፈራ ሲሆን፣ እና ፖሊሶቻችን መጠበቅ እና ማገልገል ላይ ትኩረት ሲያደርጉ አካባቢያቸን አስተማማኝ እና ጠንካራ እንደሚሆን እናውቃለን። ከእሴቶቻችን መካከል ቁልፍ የሆነው አንዱ ኗሪዎች መብታቸውን መረዳቸውን እና፣ የሕዝብ ሸክም ሂደቱን ጨምሮ ጥያቄዎች ሲኖራቸው ለእርዳታ የት መሄድ እንዳለባቸው ማረጋገጥ ነው። ከዚህ በታች ያሉት ጥያቄዎች እና መልሶች በፌደራል መንግስት ኦገስት 14፣ 2019 የወጣውን [አዲሱን የመጨረሻ የሕዝብ ሸክም መመሪያ](#) አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት የታቀደ ነው።*

**እባክዎ ያስተውሉ፣ እነዚህ ጥያቄዎች እና መልሶች *<u>የህግ ምክር ምትክ ሆነው ማገልገል የለባቸውም።</u>* የሕዝብ ሸክም መመሪያው ለነሱ ተፈጻሚ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ጥያቄዎች ያላቸው ግለሰቦች የስደተኛ ጠበቃን ምክር መጠየቅ አለባቸው፣ ወይም ለመመሪያ በከንቲባ ጽህፈት ቤት የማህበረሰብ ጉዳዮች የስደተኛ ፍትህ የህግ አገልግሎቶች (IJLS) ተቀባዮችን ያግኙ። አድራሻቸው በዚህ መገኘት ይቻላል https://dc.gov/immigration-resources።**

1. **የሕዝብ ሸክም ፈተና ምንድን ነው?**
   የፌደራል ስደተኛ ባለስልጣኖች የሕዝብ ሸክም ፈተናውን የስደተኛ ቪዛዎች እና ህጋዊ ቋሚ የመኖሪያ ሁኔታ (LPR) (የ "ግሪን ካርድ" ያላቸው) ለሚጠይቁ ሰዎች ይጠቀምበታል። የሕዝብ ሸክም ፈተናው አላማ ግለሰቡ ፤የሱ ወይም የሷ ሁኔታ አጠቃላይ ሁኔታቸውን መሰረት በማድረግ፣ ወደፊት ለድጋፍ በU.S. መንግስት ላይ ጥገኛ ሊሆን እንደሚችል ለመመዘን ነው። የፌደራል ስደተኛ ባለስልጣኖች ግለሰቡ የሕዝብ ሸክም የመሆን እድል እንዳለው ከወሰኑ፣ የግለሰቡን የቪዛ ወይም ህጋዊ ቋሚ የኗሪነት ሁኔታ ማመልከቻ ሊከለክሉ ይችላሉ።

2. **የሕዝብ ሸክም ፈተና በአሁኑ ጊዜ ብዙ ትኩረት ለምን ተሰጠው?**

---

[1] https://www.npr.org/2019/10/11/769376154/n-y-judge-blocks-trump-administrations-public-charge-rule

እስከ ኦገስት 14፣ 2019 ድረስ፣ የፌዴራል መንግስት "የሕዝብ ሸክም" የሚለውን ቃል የተረጎመው ለእርዳታ በዋነኛነት በመንግስት ላይ ጥገኛ የሆነ ሰው በማለት ነው።[2] ነገር ግን፣ የመጨረሻው የፌዴራል ሕግና መመሪያ ፣ ምንም እንኳን በዋነኛነት በነዚያ ጥቅሞች ላይ ጥገኛ ባይሆንም፣ የተወሰነ የህዝብ ጥቅማጥቅሞችን የሚቀበል ማንኛውንም ሰው እንዲያካትት በማድረግ ትርጉሙን አስፍቷል። በተጨማሪም፣ ምንም እንኳን ቀደም ሲል የሕዝብ ሸክም ፈተናው የግለሰብን የፌደራል፣ የክልል፣ እና የአካባቢ የጥሬ ገንዘብ እርዳታ ፕሮግራሞችን ( SSI እና TANF ጨምሮ)፣ እንዲሁም የMedicaid የረጅም ጊዜ እንክብካቤን ጨምሮ ለረጅም ጊዜ የተቋም እንክብካቤ የህዝብ ድጋፍ ብቻ ይመለከት የነበረ ቢሆንም፣ የመጨረሻ የፌደራል መመሪያው ይህን ዝርዝር አስፍቷል። በመመሪያው መሰረት፣ ከኦክቶበር 15፣2019 ጀምሮ ሌሎች የተለያዩ የህዝብ ጥቅማ ፕሮግራሞች፣ በ Medicaid፣ Food Stamps (SNAP) የሚሰጡ የጤና መድን ሽፋንን ጨምሮ፣ እና የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች አሁን በሕዝብ ሸክም ፈተና ውስጥ ተካተዋል። በተጨማሪ የሕዝብ ሸክም ፈተና በአሁኑ ጊዜ የቪዛ ፈቃዳቸውን ለማደስ ወይም ለመቀየር ለሚፈልጉ ሰዎች ተፈጻሚ ነው።

3. **የመጨረሻው የፌደራል ሕግ በሥራ ላይ የሚውለው መቼ ነው?**
   ለውጦቹ ኦክቶበር 15፣ 2019 በሥራ ላይ እንዲውሉ ታቅዶ ነበር፣ ነገር ግን ኦክቶበር 11፣ 2019 በሁለት የፌዴራል የወረዳ ፍርድቤቶች በተሰጠ ብሄራዊ እግድ ምክንያት ተለዋጭ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ዘግይቷል። መመሪያው ተግባራዊ የሚደረገው በተፈጻሚነት ቀኑ ላይ ወይም ከዚያ በኋላ ለተጻፉ ማመልከቻዎች እና ጥያቄዎች (ወይም፣ የሚቻል ቢሆን፣ ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ ለገቡ) ብቻ ነው። መመሪያው ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት የገቡ ማመልከቻዎች እና ጥያቄዎች፣ በመመሪያው አይገዙም። በመመሪያው መሰረት፣ ማንኛውም እነዚህ ***<u>አዲስ ጥቅማጥቅሞች</u>*** (Medicaid፣ SNAP፣ እና የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች) ከተፈጻሚነት ቀኑ ***<u>በፊት</u>*** የገቡ ከሆነ፣ እነሱ የሕዝብ ሸክም አካል እንደሆኑ ***<u>አይቆጠሩም</u>***። ከዚያ ቀን በኋላ ጥያቄ የቀረበባቸው ወይም የተገኙ ሁሉም ጥቅማጥቅሞች በስሌቱ ውስጥ ይካተታሉ።

4. **ግለሰቡ የሕዝብ ሸክም መሆኑን ለመወሰን ምን ምን ነገሮች ከቁጥር ውስጥ ይገባሉ?**
   የሕዝብ ሸክም ውሳኔ የሚመሰረተው የግለሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከት ነው፣ ይህም ቢያንስ እድሜን፣ ጤንነትን፣ የቤተሰብ ሁኔታን፣ ንብረቶች፣ ሀብቶች፣ የገንዘብ ሁኔታ፣ ትምህርት እና ክህሎቶችን የሚያካትት ነው። በአጠቃላይ፤ የአሉታ ምክናቶች ተብለው የሚቆጠሩት ከሥራ ብቃት እድሜ ማነስ ወይም መብለጥ፣[3] አንዳንድ የጤንነት ሁኔታዎች መኖር፣ የግል የጤንነት ሽፋን ያለመኖር፣ ዝቅተኛ ገቢ ወይንም ሀብት መኖር (በ 2019 ለሶስት ቤተሰብ ከፌደራል የድህነት ደረጃ 125% በታች መሆን ወይንም $26, 663 በታች መሆን)፣ ተቀጣሪ ወይንም ዋነኛ ተንከባካቢ አለመሆን፣ ዝቅተኛ የትምህርት ድረጃ መኖር፣ አነስተኛ የእንግሊዝኛ ብቃት፣ በአሁኑ ጊዜ ወይንም ቀደም ሲል የሕዝብ ጥቅማ ጥቅሞችን መጠቀም ይገኙበታል።

   ይህን ውሳኔ ለማድረግ፣ መመሪያው አንዳንድ ነገሮች የበለጠ ክብደት እንደሚኖራቸው ይናገራል - በጥንቃቄ የሚመዘኑ አሉታዊ ፍሬነገሮች የሕዝብ ሸክም ውሳኔ የማሰጠት እድል አላቸው በሌላ በኩል አወንታዊ ፍሬነገሮች አንድ ሰው የሕዝብ ሸክም እንዳልሆነ

---

[2] "የሕዝብ ሸክም ።" National Immigration Law Center (ብሄራዊ የስደተኛ ሕግ ማዕከል)። https://www.nilc.org/issues/economic-support/pubcharge/።

[3] ከ 18 እስከ 61 እድሜ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የሥራ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው ተብሎ ይውሰዷል።

እንዲቆጠር የማድረግ እድል አላቸው። ምንም እንኳን የተለዩ የህዝብ ጥቅማጥቅሞችን መቀበል አንድ ሰው ወዲያዉኑ የህዝብ ሸክም ተብሎ እንዲቆጠር የማያደርገው ቢሆንም፣ የህዝብ ጥቅማጥቅሞችን መቀበል የህዝብ ሸክም መሆኑን ለመወሰን ***<u>በጥንቃቄ ከሚመዘኑት አሉታዊ ፍሬ ነገሮች</u>*** ውስጥ ከአራቱ አንዱ እንደሆነ የመጨረሻው መመሪያ ይቆጥረዋል።

***<u>በጥንቃቄ የሚመዘኑ አሉታዊ ፍሬ ነገሮች</u>*** የሚያካትቱት፣

- ከመግቢያ ማመልከቻው ከ36 ወራት በፊት ጀምሮ ወይም በሁኔታ ማስተካከያው ተፈጻሚነት ቀን ወይም ከዚያ በኋላ፣ በ36 ወር ክፍለጊዜ ውስጥ ከ12 ወራት በላይ ጥቅማጥቅሞችን መቀበል። የህዝብ ጥቅማጥቅሞችን የተጠቀሙበትን የወራት ቁጥር ለመቁጠር አላማ መመሪያው በወር ውስጥ የተገኘውን እያንዳንዱን ጥቅማጥቅም እንደ አንድ ወር አድርጎ ይቆጥረዋል። ይህ ማለት፣ ለምሳሌ፣ አንድ ግለሰብ በአንድ ወር ውስጥ ሁለቱንም Medicaid እና SNAP ከተቀበለ፣ ግለሰቡ የህዝብ ሸክም መሆኑን ለመወሰን አላማ የግለሰቡ የጥቅማጥቅሞች አጠቃቀም ሁለት ወራት ተብሎ ይቆጠራል።
- በህዝብ ሸክም ምክንያቶች የተቀባይነት አለማግኘት (ወይም ከአገር የማስወጣት) የቀደመ ግኝት
- ግለሰቡ ስራ እንዲሰራ ፍቃድ ያለው መሆኑ ነገር ግን መቀጠሩን ማሳየ አለመቻል (የቅርብ ጊዜ ወይም የወደፊት የመቀጠር እድልን ጨምሮ) እና የሙሉ ጊዜ ተማሪ ወይም ዋና ተንከባካቢ ያልሆነ፣ እና
- ግለሰቡ ከፍ ያለ ህክምና ወይም ተኝቶ መታከምን የሚጠይቅ የህክምና ሁኔታ ያለው መሆኑ ነገር ግን የመድን ዋስትና የሌለው ወይም ለመክፈል በቂ ሀብት የሌለው እንደሆነ።

***<u>በጥንቃቄ የሚመዘኑ አወንታዊ ፍሬ ነገሮች</u>*** የህዝብ ሸክም መሆኑን ለመመርመር የሚያካትተው፣

- በ Affordable Care Act (ተመጣጣኝ የእንክብካቤ ህግ) የግብር ተቀናሽ ድጎማ የማይደረግለት የግል የጤና መድን ባሁን ጊዜ መኖር፣
- ከፌደራል የድህነት ደረጃ ቢያንስ 250 ፐርሰንት የቤተሰብ ንብረቶች/ሀብቶች መኖር፣[4] እና
- ከፌዴራል የድህነት ደረጃ ቢያንስ 250 ፐርሰንት ገቢ ኖሮት ስራ ለመስራት ወይም ለመቀጠር ፍቃድ ያለው።

በተጨማሪ፣ ምንም እንኳን "በጥንቃቄ የሚመዘን አወንታዊ ፍሬነገር" ባይሆንም እንኳን፣ የ Affordable Care Act (ተመጣጣኝ የእንክብካቤ ህግ) የግብር ተቀናሽ የሚያካትት የግል የጤና መድን ሽፋን መኖር፣ በ DC Health Link የሚገኝ ሽፋንን ጨምሮ፣ አወንታዊ ምክንያት ነው።

**5. በፌደራል የመጨረሻ መመሪያ፣ አንድ ግለሰብ የህዝብ ሸክም መሆኑን ለመወሰን የፌደራል ኤጄንሲዎች የሚያይዋቸው የህዝብ ጥቅም ፕሮግራሞች ምንድን ናቸው?**

[4] *ይመልከቱ* 2019 U.S. Federal Poverty Guidelines (ዩኤስ የፌደራል የድህነት መመሪያዎች። https://aspe.hhs.gov/poverty-guidelines

መመሪያው የህዝብ ጥቅማጥቅምን የሚተረጉመው ለገቢ መተዳደሪያ፣ እና የፌደራል ጤና፣ ስነምግብ እና የመኖሪያ ቤት ፕሮግራሞች የፌደራል፣ የክልል፣ ወይም የአካባቢ የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞችን የሚከተሉትን ብቻ ነው፡፡

- Suplemental Security Income የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI)
- Temporary Assistance for Needy Families ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ (TANF)
- Supplemental Nutritional Assistance Program ተጨማሪ የስነምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)
- እድሜያቸው ከ21 በላይ ለሆኑ ነፍሰጡር ላልሆኑ አዋቂዎች Medicaid (በጥያቄ 6 ላይ የተዘረዘረውን የተወሰኑ አይነቶች Medicaid የማያካትት)
- የመኖሪያ ፕሮግራሞች፣
    - ድጎማ የሚደረግለት የህዝብ መኖሪያ
    - ክፍል 8 በ Housing Choice Voucher Program (የመኖሪያ ቤት ምርጫ የቫውቸር ፕሮግራም) የመኖሪያ ቤት እርዳታ
    - ክፍል 8 የፕሮጀክት መሰረት ያለው የኪራይ እርዳታ
- ለገቢ መተዳደሪያ ማንኛውም የፌደራል፣ ክልል፣ አካባቢ፣ ወይም የጎሳ የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፣
    - Program on Work Employment and Responsibility (POWER) (የስራ ቅጥር እና ሃላፊነት ፕሮግራም)
    - Interim Disability Assistance (ጊዜያዊ የአካል ጉዳተኛነት እርዳታ) (IDA)፣ እና
    - General Assistance for Children (ለህጻናት አጠቃላይ እርዳታ) (GC)

6. **በመጨረሻ መመሪያው የህዝብ ሸክም ውሳኔን ለመወሰን በአሉታዊ *የማይወሰዱ* የምዝገባ ፕሮግራሞች?**

በመጨረሻው መመሪያ መሰረት፣ የሚከተሉት ፕሮግራሞች የህዝብ ሸክምን ለመወሰን እንደየህዝብ ጥቅማጥቅሞች ***አይቆጠሩም***፡

- የተወሰኑ የ Medicaid ጥቅማጥቅሞች፣
    - Medicaid ለነፍሰጡር ሴቶች
    - Medicaid ጥቅማጥቅሞች ከ21 አመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች
    - Medicaid ለድንገተኛ አደጋ የህክምና አገልግሎቶች( የድንገተኛ አደጋ Medicaid)
    - Medicaid የትምህርት ቤት መሰረት ያላቸው አገልግሎቶች፣ በ Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ህግ) (IDEA) ውስጥ የሚካተቱትን ጨምሮ
- Children's Health Insurance Program(የህጻናት የጤና መድን ሽፋን ፕሮግራም) (CHIP) ጥቅማጥቅሞች
- በአካባቢው የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው የጤና መድን ሽፋን፣
    - DC Healthcare Alliance Program (የዲሲ የሀልዝኬር አሊያንስ ፕሮግራም)
    - DC Immigrant Children's Program (የዲሲ የስደተኛ ህጻናት ፕሮግራም)
- የግል የጤና መድን ሽፋን፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፣
    - በ DC Health Link የተገዙ እቅዶች
    - ለዚህ ሽፋን የተገኙ የግብር ተቀናሾች/ድጎማዎች
- የተወሰኑ የስነምግብ ጥቅማጥቅሞች፣

- Special Supplemental Nutrition Program for Women, Infants and Children (ለሴቶች፣ ህጻናት እና ልጆች ልዩ ተጨማሪ የስነምግብ ፕሮግራም) (WIC)
- ነጻ እና ቅናሽ የትምህርት ቤት ምግቦች(የትምህርት ቤት የምሳ ፕሮግራም)
- የአደጋ ጊዜ ተጨማሪ የስነምግብ እርዳታ

- Head Start (ሄድ ስታርት)
- Healthy Start (ሄልዚ ስታርት)
- Pell Grants (ፔል ግራንትስ)
- የማህበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳት መድን
- መንግስታዊ ያልሆነ የጥሬ ገንዘብ ያለሆነ አገልግሎቶች ወይም እርዳታ፣ እንደ የቤት አልባዎች መጠለያ እና የምግብ ጓዳዎች

**7. አንድ ግለሰብ ከጥቅማቅሞቹ ለአንዱ ካመለከተ እና ነገር ግን ባይመዘገብ፣ እንደዚያም ቢሆን ያ የህዝብ ሸክም እንደሆነ ይቆጠራል?**

አዎ። በመጨረሻው መመሪያ፣ የ U.S. Department of Homeland Security (ዩኤስ የአገር ውስጥ ደህንነት ዲፓርትመንት) ግለሰቡ ለህዝብ ጥቅማጥቅሞች ያመለከተው፣ የተፈቀደለት፣ ወይም ከምዝገባው የተሰረዘው "የግለሰቡ አጠቃላይ ሁኔታዎች" ለማየት በርካታ ፍሬነገሮች ተገናዘብው መሆን ወይም አለመሆኑን ይመለከታል። የሚከተሉት ለህዝብ ጥቅማጥቅሞች ማመልከት ወይም መጠቀም ሁኔታዎች የህዝብ ሸክምን ለመመርመር ግምት ውስጥ ***አይገቡም፡***

- በአንድ ግለሰብ ልጅ ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባሎች የተፈለገ፣ ፍቃድ ያገኘ፣ ወይም የተገኘ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች፣ (ለበለጠ ዝርዝር መረጃ፣ ከታች ያለውን ጥያቄ 11 ይመልከቱ)
- በአገልግሎት አባሎች በስራ ግዴታ ላይ ባሉ ወይም በተጠባባቂ ያሉት እና ቤተሰቦቻቸው ያገኙት ጥቅማጥቅሞች፣
- በግለሰብ የተወሰደ ጥቅማጥቅሞች ግለሰቡ ከህዝብ ሸክም ውሳኔ ቀሪ በሆነው የስደተኝነት ምድብ ላይ ባለ ጊዜ የተወሰደ ፣ እና
- በውጭ አገር የተወለዱ የ ዩኤስ ዜግነት ካላቸው ወላጆች የተወለዱ አውቶማቲክ በሆነ መንገድ ዜጋ የመሆን ብቃት ባላቸው ሰዎች የተወሰደ ጥቅማጥቅሞች።

**8. እኔ Lawful Permanent Resident (ሕጋዊ ቋሚ ኗሪ) (LPR) ነኝ እና ግሪን ካርድ አለኝ። እኔ የLPR ሁኔታ ኖሮኝ ያገኘሁት ጥቅማጥቅሞች የዜግነት ማመልከቻየን ይጎዳል?**

የህዝብ ሸክም ምርመራው አስቀድሞ ህጋዊ ቋሚ ኗሪ ግለሰቦች በአጠቃላይ ተፈጻሚ አይደለም፣ እና የመጨረሻ ትእዛዙ ይህንን በማንኛውም ሁኔታ አይቀይረውም። ነገር ግን፣ ከወንጀል እንቅስቃሴ፣ ከአገር ውጭ ለረጅም ጊዜ መቆየት(ከ180 ቀኖች በላይ)፣ ወይም ህጋዊ ቋሚ ኗሪነት ሁኔታን መተው ለህዝብ ሸክም ምርመራ ተፈጻሚነት መቅረት የተወሰኑ ልዩ ምክንያቶች ናቸው።

**9. ይህ የህዝብ ሸክም መመሪያ ወደ United States (ዩናይትድ ስቴትስ) ለመሰደድ ለሚፈልግ እያንዳንዱ ሰው ላይ ተግባራዊ ነው?**

አይደለም። የሚከተሉት ግለሰቦች የህዝብ ሸክም ውሳኔዎች ላይ ተገዥ አይደሉም።

- በጊዜያዊ የጥበቃ ሁኔታ ላይ ያሉ ስደተኞች እና ግለሰቦች፣

- የህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወይም ሌሎች ከባድ ወንጀሎች የተረፉ ሰዎች
- በመመሪያው ላይ በተገለጸው ህግ ስር ጥበቃ የሚደረግላቸው የተወሰኑ ስደተኞች እና የህዝብ ባለስልጣናት፣
- የ ዩኤስ ዜግነት የሚያገኙ የተወሰኑ ከአለምአቀፍ በጉዲፈቻ የተወሰዱ እና ልጆች፣
- የተወሰኑ የAfghan (አፍጋን) እና የIraqi (ኢራቅ) አስተርጓሚ፣ ወይም Afghan (አፍጋን) ወይም Iraqi (ኢራቅ) ዜጋ በዩኤስ ወይም ለ ዩኤስ የተቀጠረ መንግስት፣
- የሁኔታ ማስተካከያ እንዲደረግ የሚያመለክቱ የተወሰኑ ከ Cuban (ኩባ) እና Haitian (ሀይቲ) የገቡ ሰዎች፣
- የሁኔታ ማስተካከያ እንዲደረግ የሚያመለክቱ የተወሰኑ Nicaraguans (ኒካራጉዋኖች) እና ሌሎች Central Americans (ሴንትራል አሜሪካውያን)፣
- የሁኔታ ማስተካከያ እንዲደረግ የሚያመለክቱ የተወሰኑ Vietnam (ቬትናም)፣ Cambodia (ካምቦዲያ) እና Laos (ላኦስ) ዜጋዎች፣
- ከአለምአቀፍ ድርጅቶች፣ የዲፕሎማቲክ ሚሽኖች (ኤምባሲዎች)፣ ወይም NATO ጋር በተያያዘ ቪዛ ለማግኘት ወይም ይዞ ለመቆየት የሚፈልጉ ስደተኛ ያልሆኑ ሰዎች፣ እና
- ከ ዩኤስ ልዩ የቀሪ መብት ለማግኘት በሚገባ ያመለከተ እና ተቀባይነት ያገኘ ማንኛም ሰው የአገር ውስጥ ደህንነት ዲፓርትመንት።

**10. ልጆቼ የህዝብ ፕሮግራም ጥቅማጥቅሞችን ቢጠቀሙ፣እኔ የህዝብ ሸክም እንደሆንኩ እቆጠራለሁ?**

አይደለም። የህዝብ ሸክም ፈተና ***በሚያመለክተው ግለሰብ*** የተወሰዱ ጥቅማጥቅሞችን ብቻ ይመለከታል እና በግለሰቡ ልጆች ወይም ሌላ የቤተሰብ አባሎች የተወሰዱ ማንኛውንም ጥቅማጥቅሞች ግምት ውስጥ አያስገባም።

**11. የሕዝብ ፕሮግራሞችን በመጠቀሜ ከአገር እንድባረር የሚያደርግበት ማንኛውም እድል አሁን ይኖራል?**

አዎ፣ ነገር ግን ይህ በጣም አልፎ አልፎ ነው እና የሚከሰተው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፣ (1) ከስደት በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ወይም የረጅም ጊዜ እንክብካቤን ሲጠቀሙ ነበር (2) እርስዎ ወይም የእርስዎ ስፖንሰር ለተገኙ አገልግሎቶች እንድትከፍሉ ተጠይቃቹ ነበር፣ እና (3) እርስዎ ወይም የእርስዎ ስፖንሰር ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆናቹም። የመጨረሻው የ ዩኤስ የአገር ውስጥ ደህነት ዲፓርትመንት የህዝብ ሸክም መመሪያ የህዝብ ሸክም ከአገር የማስወጣት ምክንያቶችን አይለውጥም።

**12. ሰዎች የህዝብ ሸክም እንዳይሆኑ ወይም የመጨረሻው ትእዝዛ ቤተሰባቸውን እንዴት እንደሚጎዳ ከተጨነቁ ምን ማድረግ ይገባቸዋል?**

የህዝብ ሸክም ሆኖ መቆጠር ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎች ያላቸው ግለሰቦች ከስደተኛ ጠበቃ ምክር ማግኘት አለባቸው። በተጨማሪ እርስዎ Mayor's Office of Community Affairs Immigrant Justice Legal Services (የከንቲባው ጽህፈት ቤት የማህበረሰብ ጉዳዮች የስደተኛ ፍትህ የህግ አገልግሎቶች) (IJLS) ተቀባዮችን ማግኘት ይችላሉ። አድራሻቸው በዚህ መገኘት ይቻላል https://dc.gov/immigration-resources።

**13. እኔ የህዝብ ፕሮግራሞችን የምጠቀም ከሆነ ቤተሰቤን ስፖንሰር ማድረግ እችላለሁ?**

ምንም እንኳን ቤተሰብዎን ወደ ዩኤስ ለማምጣት መጠየቅ ቢቹሉም፣ እርስዎ የህዝብ ፕሮግራሞችን እየተጠቀሙ ከሆነ፣ እርስዎ በገንዘብ እንደሚደግፏቸው ለማሳየት “የድጋፍ ቃለመሀላ” መጠየቅ አይችሉ ይሆናል። እርስዎ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉት፣ የስደተኛ ጠበቃ ምክር ማግኘት አለብዎ። በተጨማሪ እርስዎ Mayor’s Office of Community Affairs Immigrant Justice Legal Services (የከንቲባው ጽህፈት ቤት የማህበረሰብ ጉዳዮች የስደተኛ ፍትህ የህግ አገልግሎቶች) (IJLS) ተቀባዮችን ማግኘት ይችላሉ። አድራሻቸው በዚህ መገኘት ይችላል https://dc.gov/immigration-resources።

**14. እኔ ሰነድ አለኝ። እኔ ለልጆቹ ለ Medicaid፣ SNAP፣ ወይም ሌላ ፕሮግራሞች ካመለከትኩ፣ ሰራተኛው ለስደተኛ አፈጻጸም እኔን ሪፖርት ሊያደርገኝ ይችላል?**

አይደለም። አሁን ባለው ህግ፣ ለህዝብ ፕሮግራሞች ሲያመለክቱ የሚያጋሩት መረጃ ለስደተኛ አፈጻጸም አላማዎች ከስደተኛ እና የዜግነት አሰጣጥ አገልግሎት ጋር አይጋራም። እርስዎ ለልጅዎ ካመለከቱ፣ የልጅዎን የስደተኛ ሁኔታ ብቻ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። እርስዎ ሰነድ ከሌሎት እና ልጅዎን ወክለው ከሆነ የሚያመለክቱት፣ የራስዎን የግል የስደተኛ ሁኔታ በተመለከተ መረጃ ማቅረብ አይጠበቅብዎትም። ነገር ግን፣ ክልሎች ማመልከቻዎች፣ ውሳኔዎች፣ወይም በ ዩኤስ ውስጥ የተገኙ ጥቅማጥቅሞችን እንዲያጋሩ የሚጠይቅ መመሪያዎች ወደፊት በህጋዊ ቋሚ ኗሪ ወይም የቪዛ ለውጦች ላይ ሊደነገግ ይችላል የአገር ውስጥ ደህንነት ዲፓርትመንት።